የካቲት 13 ቀን፣ 2013 ዓ ም

ለክቡር ዶ/ር ዐብይ አህመድ፤ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚንስትር፣ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

ጉዳዩ;- ወልቃይትን፤ ጠገዴን፤ ጠለምትንና ራያን በሚመለከት የአቋም መግለጫ ደብዳቤ

ከኢትዮጵያ ውጭ ከምንኖር ተቆርቋሪዎች

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዶር ዐብይ አህመድ

እኛ ከአገር ውጭ የምንኖር ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የህወሓት/ትህነግን እጅግ የሚዘገንን ጸረ-ኢትዮጵያና ጸረ-ኢትዮጵያዊነት፤ ጸረ-ፍትሃዊነት፤ ጸረ-እኩልነት፤ አፓፊነት፤ ከሃዲነት፤ መዝባሪነት፤ ሕዝብን ከሕዝብ አናካሽነት ወዘተ ስንታገል ቆይተናል። በቅርቡ ዝነኛው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት፤ ፋኖ፤ የአማራ ልዩ ኃይል፤ የአፋር ልዩ ኃይልና ያካሄዱትን በታሪክ ሲጠቀስ የሚኖር ትግልና ድል እናደንቃለን። የፌደራሉ መንግሥት አመራር ከሕዝቡ ጋር በመናበብ ለተጫወተው ሚና ምስጋናችንን እንገልጻለን።

የዚህ ደብዳቤ ዋነኛ ትኩረት እንዲሰጠው የምንፈልፈው ትህነግ ምንም የታሪክም ሆነ ህጋዊ መነሻ ሳይኖረው በጉልበትና ስልጣንን መከታ በማድረግ ከአማራው በመቀማት ከ30 ዓመታት በላይ ይዟቸው የነበሩትና አሁን ህዝብ በከፈለው እልህ አስጨራሽ መስዋዕትነት የተመለሱት የወልቃይት፤ የጠገዴ፤ የጠለምትና የራያ የወደፊት እጣ ፋንታን የሚመለከት ነው። በተለያዩ ጊዜዎች በሚዲያ የምንሰማውና በተለይም አንዳንድ ባለስልጣናት ይህንን መስዋእት የተከፈለበትን ጉዳይ አስመልክቶ የሚሰጧቸው አስተያየቶች እጅግ አሳሳቢ ሆነው አግኝተናቸዋል። በብልጽግና ውስጥ የሚገኙና ከገዢው ፓርቲ ውጭም ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ ምሁራን፤ የሶሻል ሚዲያ አክቲቪስቶች የሚሰጡትን አስተያየቶች በአፅንኦት እየተከታተልናቸው እንገኛለን።

ሕወሓት/ትህነግ የቀሰቀሰው ጦርነትና ያካሄደው የሚዘገንን ክህደትና እልቂት የአካባቢውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደቀሰቀሰው ይታወቃል። የአማራው ክልል ሕዝብና ሌላው ኢትዮጵያዊ፤ በተለይ ጎንደሬውና ወሎየው በአንድነት ያለውን ቁሳቁስ፤ ጉልበትና ሌላ በገፍ ለፌደራሉ መንግሥት፤ በተለይ ለመከላከያው ኃይል ያበረከተበት አንዱና መሰረታዊ ምክንያት ጁንታው በወልቃይት፤ በጠገዴ፤ በጠለምትና በራያ ሕዝብ ላይ ያካሄደውን የሚታይና ገና መመርመር ያለበትን የሚዘገንን የእልቂት መጠን በማጤን፤ የአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ ከቀየው ተባሮ ወደ ሌሎች ቦታዎች የተሰደደው የሚመለስበት እድል ይፈጠርለታል፤ ተወስዶበት የነበረው አማራዊ ማንነቱና ጥንተ እርስቶቹ ወደቀድሞው ይዞታ ይመለሳሉ በሚል ስሌት መሆኑ እሙን ነው።

በእኛ ጥናትና ምርምር እንዲሁም ብዙ የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚሳዩት ወልቃይት፤ ጠገዴና ጠለምት ከብዙ መቶዎች ዓመታት በላይ በጎንደር ስር እንደ ነበሩ ይታወቃል። በተመሳሳይ ራያ ለብዙ መቶ ዓመታት በወሎ ስር ይተዳደር የነበረ አካል ነው። ታሪክን መሰረት ካደረግን እነዚህ አካባቢዎች የትግራይ ክልል አካል የሆኑት በመሳሪያ ኃይል ከተነጠቁ በኋላ ነው።

በእኛ እምነት የወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምትና ራያ የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ ለመወሰን የሚከተሉትን እዉነታዎች በማገናዘብ መሆን አለበት።

1. ትህነግ ወልቃይትን፤ ጠገዴን፤ ጠለምትንና ራያን በጉልበት የነጠቀውና የተቆጣጠረው የአማራውን እርስት ብቻ ሳይሆን ማንነቱንም ጭምር ነው። ስለዚህ የእነዚህ ቦታዎች መመለስ በዋናነት የመሬቱ መመለስ ብቻ ሳይሆን ማንነትን የማስከበር ተፈጥሯዊና ህጋዊ መብት መሆኑ ዋነኛ ታሳቢ በማድረግ መሆኑን በማጤን ነው።

2. የወልቃይት፤ የጠገዴ፤ የጠለምትና የራያ ነባር ነዋሪዎች ማንነታችን ይከበር ብለው ጥያቄ ማንሳታቸውና አሁን ደግሞ በከፈሉት መስዋእትነት ያገኙትን ነፃነት እንዲከበርላቸው ጥያቄ እያቀረቡ መሆኑን በመግንዘብም ጭምር መሆን አለበት።

3.ትህነግ/ህውሓት መሳሪያ ተጠቅሞ፤ ከውጭ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ተባብሮ፤ በመከላከያ ሰራዊቱና በአማራው ህዝብ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የማይረሳ እልቂት ፈጽሟል።

4. አካባቢው ነፃ ከወጣ በኋላ በጉግል ካርታ የሚታዩ ወደ ዘጠኝ የሚገመቱ የጅምላ መቃብሮች ተገኝተዋል። ይህ መረጃ የሚያመልከተው የትህነግ መሪዎችና ግድያ የፈጸሙ አባላት በአማራው ላይ ምን ያህል ዕልቂት እንደፈጸሙ  የሚያሳይና እልቂት የፈጸሙት ግለሰቦች በአስቸኳይ ለህግ መቅረብ እንዳለባቸው መሆኑን በመገንዘብ የክልሉና የፌደራሉ ባለሥልጣናት ለዚህ የሰብአዊ መብት ጥሰትና ፍትሃዊ መፍትሄ አስፈላጊነት ትኩረት እንዲሰጡት እናሳስባለን።

እኛ ተመራምረን የደረስንበት ግንዛቤና ድምዳሜ በቅርቡ ታላቁ ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ መምህር ታየ ቦጋለ ካቀረቡት አይለይም። ለፍትህ የቆመ ዜጋ ሁሉ ሃቁን መርህ የማድረግ ግዴታ አለበት። በአጭሩ ሃቁ እንደሚከተለው ነው።

- **ዕውነት አንድ፤** ወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምትና ራያ በዘመናት ታሪክ ውስጥ የዐማራ ማንነት መገለጫዎች ናቸው።
- **ዕውነት ሁለት፤** እነዚህ መሬቶች ሕገ መንግሥቱ ከመፅደቁ በፊት ትህነግ በጠመንጃና ሥልጣኑን መከታ አድርጎ ያለህዝብ ፍላጎት (ሪፈረንደም) በሓይል የተወሰዱ ስለነበሩ የሕገ መንግሥት ጥያቄ አይነሳባቸውም፤ ሊነሳባቸውም አይችልም። ይህ ቢሆን የባሰና ሌላ እልቂት እንደሚያስከትል መገመት እንችላለን።
- **ዕውነት ሶስት፤** ለ30 ዓመታት በወልቃይት፤ በጠገዴ፤ በጠለምትና በራያ አማራ ነኝ ማለትና አማርኛ መናገር ያስገድል ነበር። አማራዎች በቋንቋቸው እንዲማሩ፤ እንዲዳኙና እንዲተዳደሩ አይፈቀድም ነበር። በአንጻሩ መራራ እውነት፤ አገው፤ ኦሮሞ፤ አርጎባ አማራ ክልል ውስጥ በራሳቸው ይተዳደራሉ።
- **እውነት አራት፤** ከ500,000 በላይ አማሮች በገፍና በግፍ ከወልቃይት፤ ከጠገዴ፤ ከጠለምትና ከራያ ተፈናቅለዋል። የእርሻ መሬቶቻቸው ተነጥቀው ለወያኔዎች ቤተሰቦች ተከፋፍለዋል። ብዙ ሺህዎች ተሰደዋል።
- **እውነት አምስት፤** ትህነግ አማራውን ገድሎ፤ አፈናቅሎ፤ አሰድዶና አስሮ ከነባር ነዋሪዎቹ እጥፍ  የሚበልጥ ትግሬዎችን በነዚህ መሬቶች አስፍሯል። የሕዝቡን ስርጭት ቀይሮታል (Demographic change)።
- **እውነት ስድስት፤** አስር ሺህዎች አማራዎች በማንነታቸው ተጨፍጭፈዋል። በማይካድራ ከአንድ ሺህ በላይ የሚገመቱ አማራዎች የጅምላ ጭፍጨፋ ተፈጽሞባቸዋል። መረጃዎች የሚያሳዩት በሁመራ ብቻ፤ ብዙ የአማራ የጅምላ መቃብሮች ተገኝተዋል። ገና ሺህዎች እውነቶች ይወጣሉ የሚል እምነት አለን።
- **እውነት ሰባት፤** የትግራይን ክልል ይመራ የነበረው የመንደር ጁንታ በቅርቡ በመከላከያ እና በአማራው ላይ ባካሄደው ዘውግ ተኮር እልቂት በአማራውና በሌሎች ትግራይ ባልሆኑ አባላት ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ ፈጽሟል። አባላትን በሲኖ ትራክ ጨፍልቋቸዋል። ራቁታቸውን ልኳቸዋል። ገና ያልተገለጹና የሚገለጹ ግፎች ፈጽሟል። ይህንን ብልጽግና ነግሮናል። በማስረጃም አይተናል።

እንደሚታወቀው ሁሉ፤ የትግራይ ክልል "ልዩ ኃይል፤ ሚሊሺያና ፖሊስ የፌደራል ወታደሮችን፤ ፖሊሶችንና አማራዎችን" እየለዩ ጨፍጭፈዋል። "የጠለምትን፤ የወልቃይትንና የራያ የአማራ ተወላጆችን" ያለምንም ማቅማማት ልክ በሩዋንዳ

"እንተርሃምዌ" ተብሎ የሚታወቀው የጭፍጨፋ ቡድን እንዳደረገው ሁሉ፤ ህወሓት የራሱን የትግራይን ወጣቶች "ሳምሪ" በሚል ስም አደራጅቶ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ፤ ከኢትዮጵያዊያን ባህልና ልምድ ውጭ በሆነ በሚዘገንን ደረጃ ንጹህ አማራዎችን አስጨፍጭፏል።

በታሪካችን ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ደረጃ "ትግሬ ባል አማራ ሚስቱን ገድሏል። ትግሬ ሚስት አማራ ባሏን ገድላለች።"

ከዚህ ላይ አንድ የአማራውን ሰብእነት ከሰው በታች የሚያደርግ ስም በተደጋጋሚ ሲነገር ሰምተናል። ይህም "አህያ" የሚል ነው። ትህነግ ያደራጀው ገዳይ ቡድን ሳምሪ "ይህን አህያ፤ ይህችን አህያ ግደል" እያሉ በሰው ሬሳ ላይ ይፎክሩ ነበር። ይህ ስያሜ በሩዋንዳ ቱትሲዎችን "ኮክሮች (Cockroach)" የሚል ስያሜ ከሰጡት ጋር ተመሳሳይ ነው። "አህያንና ኮክሮችን" መግደል ሃጢያት ሊሆን አይችልም ማለታቸው ነው።

ከዚህ ደብዳቤ ስር ስማችን የሰፈረው ግለሰቦችና ስብስቦች ክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩን የምናሳስበው ከላይ የተጠቀሰው ግፍና በደል ከተካሄደና ሕዝብ መስዋእት ከፍሎ መሬቱን ካስመለሰ በኋላ ቀደም ሲል በትግራይ ሕዝብ ስም የተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳስጠነቀቁት ሁሉ፤ "የትግራይ ብልጽግናም ሆነ ህጋዊ የሚባሉ የትግራይ ፓርቲዎች ያለልዩነት ወልቃይትን፤ ጠገዴን፤ ጠለምትንና ራያን በተመለከተ የያዙት አቋም ከትህነግ (TPLF) በምንም አይለይም።

ይህ ተተኪነት ለአማራውና ለትግራዩ ሕዝብ አያዋጣም። የትግራይ ዘውግ አባላት ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ወደ አካባቢው ለስራ እየመጡ በዚያው መኖራቸው አግባብ እንዳለው እንቀበላለን። ይህ ሁኔታ ግን በምንም መልኩ ከመሬቱና ከጥንታዊ ነዋሪው ሕዝብ አማራነት ጋር ሊምታታ አይችልም። የፌደራሉ መንግሥት አማራውን መስዋእት አድርጎ በአማራው ጀርባ የትግራይን ብልጽግና ፓርቲ ፍላጎት አሟላለሁ የሚል አቋም ከወሰደ ይህን አቋም ሙሉ በሙሉ እንደምንቃወመው አስቀድመን እናስታውቃለን። ከላይ እንደጠቀስነው፤ ይኼ ኢ-ፍትሃዊ እርምጃ ከተካሄደ ግን ተጨማሪና አላስፈላጊ እልቂት ያስከትላል የሚል ስጋት ያለን መሆኑን እንገልጻለን።

ለማጠቃለል፤ ቀጠናው የእልቂት ቀጠና እንዳይሆን ስለምንመኝ የጥንታዊው የአማራው ሕዝብ ነዋሪዎች የማንነት መብት እንዲከበርና ወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምትና ራያ ወደ አማራው ክልል መቀላቀላቸው በፌደራል መንግስት ህጋዊ እውቅና እንዲሰጠው ከአደራ ጋር እንጠይቃለን። ትህነግ ስልጣኑንና የመሳሪያ ኃይሉን ተጠቅሞ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆችን በማስፈር ነባር ነዋሪውን በመግደል፤ በማሰደድ፤ በማፈናቀል ቁጥሩ ካሰፈረው ህዝብ በእጅጉ እንዲያንስ አድርጎ ዛሬ "የሕዝብ ድምጽ/Referendum ማካሄዱ መፍትሄ ያመጣል ብሎ ማሰብም ሆነ ማቀድ በምንም መልኩ ተቀባይነት የለውም። ይህን እርምጃ ሙሉ በሙሉ እንቃወማለን።

ሌላም የሚሰነዘር አስተያየት አለ። ይኸውም እነዚህ መሬቶች በትግራይ ክልል ይቆዩ፤ ነገር ግን ራስ ገዝ ልዩ ዞኖች ይሁኑ የሚል በማር የተለወሰ መርዝ አይነት አስተሳሰብ ሲነገር እንሰማለን። ከ30 ዓመታት በላይ በቋንቋህ እንዳትናገር፤ እንዳትቀድስ፤ ደስታህንም ሆነ ሀዘንህን እንዳትገልፅ ብሎ ማንነቱን እንዲቀይር ሲያሰቃየው ከቆየው ከህወሓት ሆነ ከተተኪው ኃይል ጋር የአስተዳደር ትስስር ይኑርህ ማለት በቀደምት ነዋሪዎቹ ላይ የደረሰውን ግፍና መከራ ጉዳይ አለማለት ብቻ ሳይሆን፤ ሲያስቡት በጣም የሚዘገንን ስለሆነ ይህንን አቋም አጥብቀን እንቃወመዋለን።

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን የወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምትና ራያ ጉዳይ  የትህነግ/ህወሓት የመሬት ነጠቃ ታላቋን ትግራይን ለማጠናከር መሆኑ መታወቅ አለበት። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ትግራይን ያስተዳድሩ የነበሩት ራስ መንገሻ ስዩም በጉዳይ በቪኦኤ የአማርኛው ፕሮግራም ተጠይቀው ከጥንት ጀምሮ የትግራይ ወሰን ወይንም ድንበር ተከዜ መሆኑን አረጋግጠው ነበር። ይህ ማለት ከተከዜ ደቡብ ያሉት ወልቃይት፤ ጠገዴና ጠለምት ከ 1983 ዓመተ ምህረት በፊት በትግራይ ስር ተዳድረው እንደማያውቁ ነው። ራያም በተመሳሳዩ ሁኔታ በትግራይ ስር ተዳድሮ እያውቅም። የህወሓት የቀድሞ ከፍተኛ አመራር የነበሩት አቶ ገብረመድህን አርአያ፤ ዶ/ር አረጋዊ በርሄና አቶ ገብሩ አስራት በተለያየ ጊዜዎች በሰጧቸው አስተያየቶች ትህነግ እነዚህን መሬቶች ከአማራው ነጥቆ በኃይል ወደ ትግራይ መጠቅለል የፈለገበት ዋነኛ ምክንያቶች መካከል በታሪክ የትግራይ እርስቶች ነበሩ ብሎ አይደለም። ምክንያቶቹ፤ አንደኛ ወደ ሱዳን መውጫ ለማግኘት፤ ሁለተኛ ለም መሬቶችን

ለመቆጣጠር የድርጅታዊ ዉሳኔ በማስተላለፍ የተፈፀመ መሆኑን በማያሻማ መልኩ መስክረዋል። የእኛም ጥናቶችና ምርምሮች በማያሻማ ደረጃ የሚያረጋግጡት ይህንኑ ሃቅ ነው።

ከመሬት ነጠቃውና ነባር ነዋሪዎችን ከቀያቸው ከማባረሩ፤ ከእልቂቱ በተጨማሪ ግፍና በደል በተጨማሪ ነዋሪው ሕዝብ ማንነቱንና ሰብአዊ ሙብቱን ተገፎ ቆይቷል። "ቋንቋህን፤ ባህልህን፤ ልምድህን፤ ማንነትህን" መተው አለብህ፤ አንተ "ትግሬ እንጅ አማራ አይደለህም" የሚል እብሪተኛነት የተሞላበት ትርክት ሲካሄድ መቆየቱን ሙሉ በሙሉ እናወግዛለን፤ እንቃወማለን።

የትግራይ ብልጽግና ፓርቲ የህወሓትን ትርክት ከተከተለ ከተተኪነት የሚለይበት አንድም ነገር ሊኖር አይችልም። ይህ ተተኪነት የሚያመጣውን መዘዝ ከግምት ሳያስገባ የፌደራሉ መንግሥት እንዲፈፀም የሚያደርግ ከሆነ እኛ ይህንን ደብዳቤ የፈረምን ግለሰቦችና ስብስቦች ለፌደራሉ መንግሥት የምንሰጠውን ድጋፍ ለመቀጠል በእጅጉ የምንቸገር መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን።

በተጨማሪ መንግስትን በጥብቅ ማሳሰብ የምንፈልገው በትህነግ እብሪት ተሰደው የነበሩት ነባር ነዋሪዎች በተፋጠነ መልኩ ከስደት የሚመለሱበትን መንገድ እንዲያመቻች ነው።

ለማጠቃለል፤  ጠቅላይ  ሚኒስቴር ዶ/ር ዐብይን፤ የፌደራሉን መንግሥት ባለሥልጣናትና የአማራውን ክልል ሃላፊዎች ትኩረት እንዲሰጡበት የምናሳስበው የወልቃይት፤ ጠገዴ፤ ጠለምትና ራያ ህዝብ ከሰላሳ አመት ጉልቆ መሳፍርት ከሌለው ግፍና ሰቆቃ እንዲሁም ማንነቱ በኃይል ተነጥቆ በኃዘንና በስቃይ ዓመታትን አስቆጥሮ በእግዚአብሔር  ፈቃድና በከፈለው መስዋዕትነት  ያገኘውን ነፃነቱንና ህዝቡ  በፈቃዱ የመረጠውን አማራዊ ማንነቱንና እርስቱ የፌዴራል መንግስት ህጋዊ እውቅና እንዲሰጠው እንጠይቃለን።

ዋናው ጉዳይ፤ የመሬት ባለቤትነት ብቻ አለመሆኑን ጭምር ለማስገንዘብ እንወዳለን። ይህም ፍትሀዊና ዘላቂ መፍትሄ ያመጣል ብለን እናምናለን። ለዘመናት በትህነግ አፓርታይድ አገዛዝ የተንገላታውን የወልቃይትን፤ የጠገዴን፤ የጠለምትንና የራያን ህዝብ እንባ ሊያብስ የሚችል ሥራ እንደሚሠራ ተስፋ እናደርጋለን።

## <u>ከኢትዮጵያ ውጪ የሚኖሩ ዜጎችና የተለያዩ ድርጅቶች አባላት፤</u>

1. ዶ/ር ካሳ ከበደ
2. ዶ/ር አክሎግ ቢራራ
3. ፕሮፌሰር ከበደ ገሰስ
4. ፕሮፌሰር  ኃይሌ ላሬቦ
5. ዶ/ር ብርሃኑ አበጋዝ
6. ፕሮፌሰር ብርሃኑ መንግስቱ
7. ዶ/ር አልማዝ ዘውዴ
8. ዶ/ር ስዩም ሰለሞን
9. ፕሮፌሰር አለምአንተ ገ/ሥላሴ
10. ፕሮፌሰር ጥላሁን እንየው
11. አቶ አስማማው እጅጉ
12. ኢንጂነር ነጋሽ ገብሬ
13. አቶ ከፈለኝ አስረስ
14. መ/አ አያልሰው ደሴ
15. ዶ/ር አምባቸው ወሮታ
16. ዶ/ር ነጋሽ አምሳሉ
17. ዶ/ር ሽፈራው ገሰሰ
18. አቶ ለይኩን ካሳሁን
19. አቶ ከፍያለው መንገሻ
20. ዶ/ር ታደለ እውነቱ
21. አቶ ዘርጋባቸው ዘውዴ
22. አቶ ዔፍሬም ው/ሰንበት
23. አቶ ተክሌ ይሻው
24. አቶ ስለሺ ጥላሁን
25. አቶ ግርማ ተፈራ
26. አቶ በሀይሉ አሸናፊ
27. አቶ መኮንን ሐ/ዮሃንስ
28. ዶ/ር መስፍን አለማየሁ
29. ው/ሮ ሙሉመቤት ረታ
30. አቶ ወይንጉስ ደበበ

31. ኢንጂነር ሞገስ ብሩክ
32. ኢንጂነር ዳንኤል ካሳ
33. አቶ ግርማ መንግስቱ
34. አቶ ዘውገ ገድሉ
35. አቶ ግርማ ይስማው
36. ቀሲስ ዓስተራይ ጽጌ
37. አቶ ወርቅዓለም ዘውዱ
38. አቶ ሊቁ እጅጉ
39. ወ/ሮ ራሄል ነጋ
40. አቶ ጠና አለመየሁ
41. አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው
42. ወ/ሮ ማራኪ ውሂብ
43. አቶ ቀራቾ ገለታ
44. አቶ አባተ ካሳ
45. አቶ ኢያሱ አያልቅበት
46. አቶ አበጀ ተሰማ
47. አቶ ደጀኔ ወርቅነህ
48. አት ሙላት እሸቱ
49. አቶ መስፍን መኮነን
50. አቶ መኮነን ዶያሞ
51. አቶ ሙሉጌታ አቦሰጥ
52. አቶ ሙሉገታ ፈለቀ
53. ዶ/ር ታደለ ዓለሙ
54. ፕሮፌሰር አቻምየለህ ደበላ
55. ዶ/ር አበበ ገላጋይ
56. አቶ አለሙ ያይኔ
57. ዶር ገብርዬ ሩፋኤል
58. አቶ ግርማ ተፈራ
59. እንጂኔር ግርማ ይስማው
60. አቶ ኪዳኔ ማውሻ
61. አቶ ኮነ ፍስሃ
62. አቶ ውብሸት ወንድሙ
63. አቶ ዳኛቸው ተሾመ
64. እንጂኔር ዘውዱ በላይ
65. ወይዘሮ ፅጌረዳ ሙሉጌታ
66. አቶ ጸሃይ ደመቀ
67. አቶ መሳይ አንዳርጌ
68. አቶ ቴዎድሮስ አበራ
69. ው/ሮ አበባ አበበ
70. አቶ ሀይሌ አበበ
71. አቶ ሙሉጌታ ማንደፍሮ
72. አቶ ወንድወሰን ካሳዬ
73. ው/ሮ ሙሉወርቅ
74. እንጂነር ወርቁ አደላ
75. አቶ በትሩ ገ/እግዚአብሄር
76. አቶ ይበቃል ያረጋል
77. ዶ/ር አስረሱ ምስክር
78. አቶ አለም ወንድማገኝ
79. አቶ ደመቀ አዲሴ
80. አቶ ሰለሞን ታደሰ
81. አቶ አሰግድ ሸነገለኝ
82. አቶ ግብረክርስቶስ ሃ/ስላሴ
83. አቶ ፍቅሩ ዘውዴ
84. ፕሮፌሰር ውሰኔ ይፍሩ
85. ው/ሮ ሙሉ ካሳ
86. ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ
87. አቶ ኪሩቤል አሰግድ
88. አቶ አቤል አሰግድ
89. አቶ እንዳልካቸው ሸነገለኝ
90. አቶ ጌታቸው ምትኩ
91. ዶ/ር ሙሉአለም ጥላሁን
92. አቶ ነቢዩ ኤልያስ
93. አቶ ለማ አታክልቴ
94. አቶ ሰለሞን ጀማነህ
95. ዶ/ር ኤርሚያስ ሺኩር
96. አቶ ጌድዮን ሙጬ
97. አቶ ሳህል ው/ጊዮርጊስ
98. አቶ ሙሉጌታ ፈለቀ
99. አቶ ብርሀኑ አለሙ
100. ወይዘሪት ትግስት እውነቴ
101. ወይዘሪት ሳራ ውነቴ
102. አቶ ታደሰ ጌታሁን
103. ወ/ሮ አፀደ ተገኝ
104. ወ/ሮ ሰርካለም ነጋሽ
105. አቶ አለምሸት ደምላሽ
106. አቶ የሸጥላ ፈለቀ
107 አቶ ቢሹ ማሞ
108 ዶ/ር ኤፍሬም ዓለማየሁ
109 ዶ/ር ወርቁ ኃ/ማርያም

ግልባጭ:

ለኢፌድሪ ፕሬዝዳንት፣ ወ/ሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ

ለክቡር አቶ ደመቀ መኮንን፣ ም/ጠቅላይ ሚ/ርና የውጭ ጉዳይ ሚንስትር

ለክቡር አቶ ታገሰ ጫፎ፤ ለኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

ለክቡር አቶ አደን ፋራህ፤ የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

ለአቶ አገኘሁ ተሻገር፣ የአማራ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር

ለክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው፤ የጠ/ሚ/ር የደህንነት አማካሪ

ለክቡር አምባሳደር ፍጽም አረጋ፤ የኢትዮጵያ አምባሳደር፤ ዋሺንግተን ዲሲ፤

ለዶር ገበያው ካሳ፤ የአማራ ምሁራን መማክርት ጉባኤ ሊቀ መንበር፤ ባህር ዳር፤ ኢትዮጵያ